# የበጀት አጭር መግለጫ

Montgomery County Public Schools

# ስለትምህርት ቦርድ የበጀት ጥያቄ ፈጣን እውነታዎች

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ለ(2014–2015) የትምህርት አመት የ$2.3 ቢልዮን የመንቀሳቀሻ በጀት አቅርቧል። በጀቱ ከዚህ አመት በጀት በ4 በመቶ ይበጣል የስቴት ህግ ከሚጠይቀውም አነስተኛ የገንዘብ ገደብ ልክ በ2.5 በመቶ በላይ ነው። ይህ በጀት MCPS ለሁሉም ተማሪዎች በአለም ደረጃውን ለጠበቀ ትምህርት መዳረሻ ማቅረብ መቀጠል የሚያስችለው ሲሆን—

» የምዝገባ አድገቱን እያስተዳደረ

» የግኝት ክፍተቶችን ለማጥበብ መዋእለ ነዋይ ፈሰስ እያደረገ፣

» ተማሪዎቻችንን ለወደፊት ያዘጋጃል።

## በፋይዳዎች የሚመራ በጀት

ይህ በጀት የማህበረስባችንን ፋይዳዎች ያንፀባርቃል እናም የሚያተኩረው የትምህርት ቦርድ፣ ወላጆች፣ የት/ቤት ሰራተኞች፣ እና የማህበረሰብ መሪዎች አሳሳቢ ናቸው ብለው በሚነግሩን ላይ ነው። ከበጀቱ ዋና ዋናዎቹ መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

» በድህነት ይበልጥ ለተጠቁት ለ67 ኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች ተጨማሪ መገልገያዎች ማቅረብን መቀጠል

» $21 ሚሊዮን የሚደርስ ለ276 አዲስ የማስተማርና የስራ ቦታዎች ሆኖ፣ 2,721 ተጨማሪ ተማሪዎች የሚያገለግልና English for Speakers of Other Languages (እንግሊዘኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች) (ESOL) እና Special Education (ልዩ ትምህርት) አገልግሎቶች የሚጨምር።

» $140,000 ለሁለት ተጨማሪ ቅድመ-ሙአለህፃናት መማርያ ክፍሎች ችግር ላላቸው ቤተሰቦች

» $3 ሚልዮን ቴክኖሎጂን በመማርያ ክፍል ለማስፋፋት ለአዳዲስ ታብሌቶችና መሳርያዎች እንዲሁም አዲሱን የስቴት ግምገማዎች ለማስተዳደር

» $800,000 እስከ 250 የሚደርሱ በጣም ውጤታማ፣ አኩሪ ተሞክሮ ያላቸው መምህራን ከፍተኛ ችግር ወደ አላቸው ት/ቤቶች የሚዘዋወሩ ወይ እዚያው ለሚቅጥሉ መምህራን ማበረታቻ “Career Lattice” ፕሮግራም የሚውል

» $1 ሚልዮን አካባቢ ለተጨማሪ የሂሳብና የምንባብ መምህራን በነዚህ መሰረታዊ መስኮች ተማሪዎች የበለጠ ትግል በሚያደርጉባቸው ስምንት የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች

» ከ$1.4 ሚልዮን በላይ የESOL ተማሪዎች ቁጥር እድገት ጎልቶ በሚታይባቸው በ21 የመካከለኛ ት/ቤቶች የESOL አገለግሎት ለማሻሻል

» $1.2 አካባቢ የተማሪ ድጋፍ ሞዴል ለማሻሻል የበርካታ አመታት ጥረት ለማስጀመር የሥራ ጫናን ለማቃለል በሚመጡ አመታት የስራ ቦታዎች መጨመሩ የተጠበቀ ሆኖ፣ እነዚህ ገንዘቦች 5.5 የኤሌሜንታሪ ት/ቤት አማካሪዎች፣ 5 የት/ቤት ሳይኮሎጂስቶች፣ እና 5 ተማሪ ፔርሶኔል ሰራተኞች ያስጨምራሉ።

» ከ$2 ሚልዮን በላይ የመምህራን መሪዎች ለማሰልጠን እና ለማስተባበር ተጨማሪ ጊዜ ለመስጠት

» የማህበረሰብ ሽርክናዎች ለማሻሻልና ጥብቅ (wraparound) ጤንነትና የደህንነት አገልግሎቶች ለተማሪዎችና ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ከትምህርት በኋላ ፕሮግራሞች ማቅረቢያ ገንዘብ

በቦርዱ ስለቀረበ በጀት በMCPS ድርጣብያ www.montgomeryschoolsmd.org “Operating Budget” በመፈለግ ይበልጥ መማር ይችላሉ። በጀቱ አሁን በMontgomery County ስራ አስፈፃሚ እና በMontgomery County ምክር ቤት እጅ ይገኛል። ሀሳብዎን ከነሱ ጋር ይጋሩ፡-

» Montgomery County ስራ አስፈፃሚ Isiah Leggett (አዛያህ ሌጌት):- ocemail@montgomerycountymd.gov፣ 240-777-2500

» Montgomery County ምክር ቤት፡- county.council@montgomerycountymd.gov፣ 240-777-7900

# የበጀት አጭር መግለጫ

## Montgomery County Public Schools
# የግኝት ክፍተትን ለመዝጋት የመማርያ ክፍሎችን መጠን መቀነስ

Montgomery County የትምህርት ቦርድ ለሚመጣው የትምህርት አመት (2014–2015) የ$2.3 ቢልዮን የስራ መስኬጃ በጀት ማሳሰቢያ አቅርቧል። በጀቱ ከዚህ አመት በጀት በ4 በመቶ ይበጣል የስቴት ህግ ከሚጠይቀውም አነስተኛ የገንዘብ ገደብ ልክ በ2.5 በመቶ በላይ ነው። ይህ በጀት MCPS የምዝገባ አድገቱን እያስተዳደረ ለሁሉም ተማሪዎች በአለም ደረጃውን ለጠበቀ ትምህርት መዳረሻ ማቅረብ መቀጠል ያስችለዋል። በተጨማሪ በጀቱ MCPS የግኝትን ክፍተት ለማጥበብ እና ተማሪዎችን በወደፊታቸው እንዲበለፅጉ ለማዘጋጀት በሚያስችሉት ቁልፍ መስኮች ስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰስ ያደርጋል።

ከስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰስ መስኮች አንዱ በምንባብና በሂሳብ ትግል በማካሄድ ላይ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር የሚሰሩ ተጨማሪ መምህራን ለማቅረብ የበርካታ አመት ጥረት ነው።

## ፍላጎቱ

ባጠቃላይ፣ የMontgomery County Public Schools ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ በመስራት ላይ ይገኛሉ ዲስትሪክቱም በምረቃ መጠን፣ በላቀ ደረጃ በተመደቡ (Advanced Placement) አፈፃጸም፣ በአነስተኛ ክፍሎች በማንበብ ችሎታን በመሳሰሉ ቁልፍ መስኮች የግኝትን ክፍተት በማጥበብ ረገድ ጥሩ ውጤት እያሳየ ነው። ነገር ግን፣ በሌሎች መስኮች፣ እነዚህ ክፍተቶች እነበሩበት ደረጃ ላይ ናቸው አንዳንዶቹ እንዲያውም ብሶባቸዋል።

ለምሳሌ፣ 11ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ አልጄብራ 2ን በስኬት የሚፈፅሙ የMCPS ተማሪዎች መቶኛ ባለፉት በርካታ አመቶች ማደጉን ቀጥሏል። ቢሆንም፣ ይህን ምእራፍ የሚደርሱበት የነጭ እና የእስያን ተማሪዎች መቶኛ የአፍሪካን አሜሪካንና የሂስፓኒክ ተማሪዎች እጥፍ ነው። ይህም ክፍተት ትርጉም ባለው መጠን አልጠበበም።

## ፕላኑ

የቦርዱ በጀት 15 የ3ኛ ደረጃ የእንግሊዝ ቋንቋ ስነጥበባትና የሂሳብ የትኩረት መምህራን ለመጨመር $1 ሚሊዮን አካባቢ አካትቷል። እነዚህ መምህራን የአሀዝ መረጃዎቹ ፍላጎቱን በሚያሳዩበት የ2ኛ ድረጃ ት/ቤት የክፍል ተማሪዎችን ቁጥር ይቀንሳሉ እናም በትግል ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የበለጠ ግላዊ ትምህርት ያስችላል።

ይህ ሙአለንዋይ ከዚህ ቀደም ተጨምረው በነብሩ ቦታዎች ላይ ይገነባል፣ 17 ቦታዎች በDowncounty Consortium 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና 6 ቦታዎች ትምህርትን እንዲያግዙ በ2014 በጀት አመት በWatkins Mill፣ Springbrook እና በGaithersburg 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያካትቱ። በተጭማሪ፣ በ2014 በጀት አመት፣ የትምህርት ቦርድ በMCPS የመካከለኛ ት/ቤቶች በእንግሊዘኛና በሂሳብ የተማሪ መጠን በክፍል ለመቀነስ 30 የትኩረት መምህራንን ጨምሯል።

የቦርዱ በጀት በተጨማሪ የላቀ ፍላጎት ላላቸው ት/ቤቶች ተጨማሪ መገልገያዎች የማቅረብ የረዥም ግዜ ጥረትም ይቀጥላል። ለምሳሌ፣ ከአስር አመት በላይ፣ MCPS፣ ለ67ቱ በድህነት ይበልጡኑ ለተጠቁ የኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች፣ ለያንዳንዳቸው በአማካይ $1.9 ሚልዮን ሰጥቷል። እነዚህ ገንዘቦች፣ ባብዛኛው፣ በመማርያ ክፍል የተማሪ መጠን ለመቀነስ አገልግሎት ላይ ውለዋል።

## እወቁ/ተማሩ፣ ተገናኙን

በቦርዱ ስለቀረበ በጀት በMCPS ድርጣብያ www.montgomeryschoolsmd.org “Operating Budget” በመፈለግ ይበልጥ መማር ይችላሉ። በጀቱ አሁን በMontgomery County ስራ አስፈፃሚ እና በMontgomery County ምክር ቤት እጅ ይገኛል። ሀሳብዎን ከነሱ ጋር ይጋሩ፡

- Montgomery County ስራ አስፈፃሚ Isiah Leggett (አዛያህ ሌጌት): ocemail@montgomerycountymd.gov፣ 240-777-2500Montgomery County ምክር ቤት
- Montgomery County ምክር ቤት፡ county.council@montgomerycountymd.gov፣ 240-777-7900



MCPS

የበጀት
አጭር መግለጫ

# Montgomery County Public Schools
# በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሙአለንዋይ ፈሰስ

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ለ(2014–2015) የትምህርት አመት የ$2.3 ቢልዮን የመንቀሳቀሻ በጀት አቅርቧል። በጀቱ ከዚህ አመት በጀት በ4 በመቶ ይበጣል የስቴት ህግ ከሚጠይቀውም አነስተኛ የገንዘብ ገደብ ልክ በ2.5 በመቶ በላይ ነው። ይህ በጀት MCPS የምዝገባ አድገቱን እያስተዳደረ ለሁሉም ተማሪዎች በአለም ደረጃውን ለጠበቀ ትምህርት መዳረሻ ማቅረብ መቀጠል ያስችለዋል። በተጨማሪ በጀቱ MCPS የግኝትን ክፍተት ለማጥበብ እና ተማሪዎችን በወደፊታቸው እንዲበለፅጉ ለማዘጋጀት በሚያስችሉት ቁልፍ መስኮች ስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰስ ያደርጋል።

ከስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰስ መስኮች አንዱ፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ግኝት ማሻሻል ነው።

## ፍላጎቱ

በዚህ አመት፣ ከMCPS 13.6 በመቶዎቹ English for Speakers of Other Languages (እንግሊዘኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች) (ESOL) አገልግሎቶች ይቀበላሉ። ይህ ቁጥር ባለፈው አመት ብቻ ከ35 በመቶ በላይ አድጓል።

የESOL ተማሪዎቻችን ግኝት በተወሰኑ አካባቢዎች ሲያድግ፣ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ትርጉም ያላቸው የአፈፃጸም ክፍተቶች አሁንም አሉ። የተወሰኑ ከፍተኛ ክፍተቶች የሚታዩት በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ነው።

ለምሳሌ፣ በ8ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ፣ከMCPS ተማሪዎች 60 በመቶ ሊደርሱ የሚችሉ ተማሪዎች አልጄብራ 1ን በC ወይም ከዚያ በላይ አልፈውታል። ቢሆንም፣ ለESOL ተማሪዎች፣ 19 በመቶ ብቻ ነበር።

## ፕላኑ

በዚህ መስክ የሚጠበቀውን እድገት ለመጠበቅ 8 የESOL የስራ ቦታዎች ለመጨመር የቦርዱ በጀት ጥያቄ $500,000 ይዟል።

የESOL ተማሪዎች አፈፃፀምን ለማሻሻል የበርካታ አመት ጥረት ለመጀመር ቦርዱ በተጨማሪ $1.45 ሚሊዮን ሙአለንዋይ ፈሰስ ያደርጋል። ገንዘቦቹ ስራ ላይ የሚውሉት ለ10.5 የስራ ቦታዎች ሆነ ከፍታኛ የESOL ህዝብ ብዛት ያላቸው 21 የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲጋሩት ይደረጋል።

እነዚህ የስራ ቦታዎች ት/ቤቶችን ትምህርትን ይበልጥ ግላዊ በማድረግ፣ አሀዞችን በመተንተን፣ በተለይም በእንግሊዘኛ ችሎታ ማሳየት የጀመሩ ነገር ግን እንደ ምንባብና ሂሳብ በመሳሰሉ በመሰረታዊ አካዴሚያዊ መስኮች ትርጉም ያለው መሻሻል ለማያሳዩ የESOL ተማሪዎችን ለማሳተፍ የትምህርት ዝግጅት በማድረግ ያግዛሉ።

## እወቁ/ተማሩ፣ ተገናኙን

በቦርዱ ስለቀረበ በጀት በMCPS ድርጣብያ www.montgomeryschoolsmd.org "Operating Budget" በመፈለግ ይበልጥ መማር ይችላሉ። በጀቱ አሁን በMontgomery County ስራ አስፈፃሚ እና በMontgomery County ምክር ቤት እጅ ይገኛል። ሀሳብዎን ከነሱ ጋር ይጋሩ፡-

- Montgomery County ስራ አስፈፃሚ Isiah Leggett (አዛያህ ሌጌት):- ocemail@montgomerycountymd.gov፣ 240-777-2500
- Montgomery County ምክር ቤት፡- county.council@montgomerycountymd.gov፣ 240-777-7900



MCPS

# የበጀት አጭር መግለጫ

## Montgomery County Public Schools
## በመምህራን አመራርና ስልጠና የሙአለነዋይ ፈሰስ

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ለ(2014–2015) የትምህርት አመት የ$2.3 ቢሊዮን የመንቀሳቀሻ በጀት አቅርቧል። በጀቱ ከዚህ አመት በጀት በ4 በመቶ ይበጣል የስቴት ህግ ከሚጠይቀውም አነስተኛ የገንዘብ ገደብ ልክ በ 2.5 በመቶ በላይ ነው። ይህ በጀት MCPS የምዝገባ አድገቱን እያስተዳደረ ለሁሉም ተማሪዎች ለአለም ደረጃውን ለጠበቀ ትምህርት መዳረሻ ማቅረብ መቀጠል ያስችለዋል። በተጨማሪ በጀቱ MCPS የግኝትን ክፍተት ለማጥበብ እና ተማሪዎችን በወደፊታቸው እንዲበለፅጉ ለማዘጋጀት በሚያስችሉት ቁልፍ መስኮች ስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰስ ያደርጋል።

ከስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰስ መስኮች አንዱ፣ እጅግ ውጤታማ፣ ተሞክሮ ያላቸውን መምህራን በሉበት እንዲቀጥሉ ወይም ከፍተኛ ችግር ወዳላቸው ት/ቤቶች እንዲዛወሩ የሚያበረታታ፣ አዲሱ የCareer Lattice ፕሮግራም የሚያካትተው፣ የመምህራን አመራር ነው።

### ፍላጎቱ

Montgomery County Public Schools በሀገሪቱ ውስጥ አሉ ከሚባሉት የላቁ መምህራን የተወሰኑ አሉት እነሱም MCPS ጠንካራ ስርአት እንዲኖረው ያደረጉት የጥምረት አካል ናቸው። እጅግ በጣም ውጤታማ፣ አኩሪ ተሞክሮ ያላቸውን መምህሮቻችንን ከራሳቸው መማርያ ክፍል ውጭ እውቀታቸውንና ተክህሎሆቶቻቸውን እንዲያጋሩ እድሉን ልንሰጣቸው እንፈልጋለን።

በተጨማሪም ት/ቤቶቻችን እጅጉን ከላቁት መምህሮቻችን የትምህርት አመራር እንዲጠቀሙም ፍላጎታችን ነው ይህ በድህነት በተጠቁት አናም በዲስትሪክቱ እጅግ በጣም የሰፋ የግኝት ክፍተት ባላቸው ትምህርት ቤቶቻችን በተለይ እውነት ነው።

### ፕላኑ

የቦርዱ የበጀት ጥያቄ ከMontgomery County የትምህርት ማህበር ጋር በመተባበር የተተለመውን፣ አስተማሪዎችን "lead teacher" (መሪ መምህር) ደረጃ ለማግኘት ማመልከቻ እንዲያቀርቡ እድል የሚሰጣቸውን "Career Lattice" የተባለውን ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ $800,000 ይዟል።

በCareer Lattice፣ የመሪ መምህር ስያሜ ያገኙ መምህራን ከፍተኛ ችግር አላቸው ተብለው በታወቁ ት/ቤቶች በት/ቤት በተመሰረተ የአመራር ቦታ ወስደው የ$2,000 ማበረታቻ ደሞዝ ይሰጣቸዋል። ይህ፣ ከቦርዱ በጀት ጥያቄ $500,000 ይዟል።

የተቀረው $300,000 እያንዳንዳቸው እስከ $3.000 የሚደርሱ የእድሳት ስጦታ ሆነው፣ በግኝት ክፍተት በመዝጋት ላይ ያተኮሩ ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን ለማካሄድ እንዲውሉ፣ መሪ መምህራን ሊያመለክቱባቸው ይችላሉ።፣

የቦርዱ የበጀት ጥያቄ፣ የመገልገያና የሰራተኛ ስልጠና መምህራን የመሳሰሉ—በኤሌሜንታሪና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የተመሰረቱ መሪዎችን ለማስተባበር፣ ለማሰልጠን፣ እና ለመቆጣጠር የበለጠ እድል ለመስጠት በተጨማሪ $1.95 ሚልዮን ያካትታል።

### እወቁ/ተማሩ፣ ተገናኙን

በቦርዱ ስለቀረበ በጀት በMCPS ድርጣብያ www.montgomeryschoolsmd.org "Operating Budget" በመፈለግ ይበልጥ መማር ይችላሉ። በጀቱ አሁን በMontgomery County ስራ አስፈፃሚ እና በMontgomery County ምክር ቤት እጅ ይገኛል። ሀሳብዎን ከነሱ ጋር ይጋሩ፡

- Montgomery County ስራ አስፈፃሚ Isiah Leggett (አዛያህ ሌጌት):- ocemail@montgomerycountymd.gov፣ 240-777-2500
- Montgomery County ምክር ቤት፡- county.council@montgomerycountymd.gov፣ 240-777-7900



MCPS

**የበጀት**
**አጭር መግለጫ**

Montgomery County Public Schools

# የተማሪ ድጋፍ ሞዴል ማሻሻል

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ለመጪው የትምህርት አመት (2014–2015) የ$2.3 ቢልዮን የስራ ማስኬጃ በጀት ረቂቅ አቅርቧል። በጀቱ ከዚህ አመት በጀት በ4 በመቶ ይበልጣል በስቴት ህግ መሰረት ከሚፈለገው አነስተኛ የገንዘብ እርከንም ልክ በ2.5 በመቶ ይበልጣል። በጀቱ MCPSን የምዝገባ እድገቱን እየተቋቋመ ለሁሉም ተማሪዎች የአለም ደረጃ ትምህርት መዳረሻ መንገድ እንዲያቀርብ ያስችለዋል። በተጨማሪም በጀቱ MCPS የግኝት ክፍተቶችን ለማጥበብና ተማሪዎች በወደፊታቸው እንዲበለፅጉ ለማዘጋጀት በሚያስችሉት ቁልፍ መስኮች ስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰስ ያደርጋል።

የስልታዊ ሙአለነዋይ ፈሰስ አንዱ መስክ የአማካሪዎችን፣ ሳይኮሎጂስቶችን፣ እና pupil personnel workers (የተማሪ ፐርሶኔል ሰራተኞች) (PPWs)ን የሚያካትት ቁልፍ የሰራተኛ አባላት ብዛት በሚያሳድግ የሁለገብ የተማሪዎች አገልግሎቶች ሞዴል አማካይነት የተማሪዎችን ድጋፍ ማሻሻል ነው።

## ፍላጎቱ

የተማሪዎቻችንን ትምህርታዊና ትምህርታዊ ያልሆኑ ፍላጎቶችን ለመለየትና ድጋፍ ለመስጠት እንዲሁም ስኬታማ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ዜጎች እንዲሆኑ የሚያስፈልጓቸውን ማህበራዊና ስሜታዊ ክህሎቶች እንዲያገኙ ለማገዝ አማካሪዎች፣ ሳይኮሎጂስቶች፣ እና PPWዎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

በአስቸጋሪ የኤኮኖሚ ጊዜያት፣ MCPS የሰራተኛ መቅጠር ደረጃን በዚህ ቁልፍ መስክ ከምዝገባ እድገት ጋር ማመጣጠን አልቻለም ነበር። ተማሪዎችን በተሻለ ለመያዝና የማህበራዊና የስሜታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማርካት፣ MCPS የአማካሪዎች፣ የሳይኮሎጂስቶች፣ እና የPPWዎች የስራ/ጉዳዮች ጫና መቀነስ መቻል አለበት።

## ፕላኑ

የቦርዱ የበጀት ጥያቄ የተማሪ ድጋፍ ሰራትኞች ለመጨመርና የስራ ጫና መቀነሻ የበርካታ አመት ፕላን ለማስጀመር $1.2 ሚልዮን ያካትታል። እነዚህ ገንዘቦች የሚጨምሩት—

- 5.5 የኤሌሜንታሪ ት/ቤት አማካሪዎች
- 5 የት/ቤት ሳይኮሎጂስቶች፣ እና
- 6 pupil personnel workers (የተማሪ ፔርሶኔል ሰራተኞች)።

እነዚህ የስራ መደቦች የሚሰራጩት ከት/ቤት ምዝገባ እና ከ2ኛ ደረጃ ት/ቤት አቋርጠው የሚወጡትንና በቀሪነት የሚመዘገቡ፣ ከት/ቤት ወደ ት/ቤት እንቅስቃሴ፣ እና ከመታገድ መጠኖች ጋር የተያያዙ የተለያዩ ታሳቢዎችና አሀዞች በመመስረት ነው። እጅግ አስቸኳይ ፍላጎቶች ያሏችውን ት/ቤቶች ለመለየት እነዚህ ተለዋዋጭ አሀዞች ይመዘናሉ።

እነዚህ ቦታዎች አገለሎቶችን የሚያቃኑ እና ተማሪዎቻችን ባፋጣኝ፣ በውጤታማነት፣ እና በሚያረካ ሁኔታ የሚፈልጓቸውን ድጋፎች የሚሰጡ የCoordinated Student Services Teams (የተቀነባበሩ የተማሪ አገልግሎቶች ቡድኖች) ውጤታማ ገብረቶችን ይደግፋሉ።

## ይወቁ/ይማሩ፣ ሁልግዜ ይገናኙን

ስለ ቦርዱ የበጀት ረቂቅ የበለጠ ለመማር በMCPS ድርጣብያ በwww.montgomeryschoolsmd.org፣ "Operating Budget"ን ይፈልጉ። በጀቱ አሁን በMontgomery County ስራ አስፈፃሚ እና በMontgomery County ምክር ቤት እጅ ይገኛል። ሀሳብዎን ከነሱ ጋር ይጋሩ፡

- Montgomery County ስራ አስፈፃሚ Isiah Leggett (አይዛያ ሌጌት): ocemail@montgomerycountymd.gov, 240-777-2500
- የMontgomery County ምክር ቤት፡ county.council@montgomerycountymd.gov, 240-777-7900

# የበጀት አጭር መግለጫ

## Montgomery County Public Schools
## ለማገልገል መተባበር ልጆቻችን

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ለ(2014–2015) የትምህርት አመት የ$2.3 ቢልዮን የመንቀሳቀሻ በጀት አቅርቧል። በጀቱ ከዚህ አመት በጀት በ4 በመቶ ይበጣል የስቴት ህግ ከሚጠይቀውም አነስተኛ የገንዘብ ገደብ ልክ በ2.5 በመቶ በላይ ነው። ይህ በጀት MCPS የምዝገባ አድገቱን እያስተዳደረ ለሁሉም ተማሪዎች በአለም ደረጃውን ለጠበቀ ትምህርት መዳረሻ ማቅረብ መቀጠል ያስችለዋል። በተጨማሪ በጀቱ MCPS የግኝትን ክፍተት ለማጥበብ እና ተማሪዎችን በወደፊታቸው እንዲበለፅጉ ለማዘጋጀት በሚያስችሉት ቁልፍ መስኮች ስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰስ ያደርጋል።

ከስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰስ መስኮች አንዱ፣ የተማሪዎቻችንና የቤተሰቦቻቸውን ፍላጎቶች ልንሟላ እንድንችል፣ ወላጆችን ለማጠናከርና ሽርክናዎች ለመገንባት የሚያስችሉን የማህበረሰብ ተሳትፎና የትብብር ጥረት መደገፍ ነው።

## ፍላጎቱ

Montgomery County Public Schools የተማሪዎቹን የትምህርት ፍላጎቶች የሚሟላት ሀይለኛ/ከፍተኛ ስም አለው። የዲስትሪክቱ ምዝገባ እያደገ በመጣ ቁጥር ግን፣ እኛ፣ ብቻችንን፣ ልንወጣቸው የማንችላቸው ድጋፎችና አገልግሎቶች የሚፈልጉ ተጨማሪ ተማሪዎች ወደ MCPS እየመጡ ነው።

ባለፉት አመታት፣ MCPS፣ የተማሪዎችንና የቤተሰቦቻቸውን ሁለንተናዊ ፍላጎቶች ለሚሟላት፣ ከካውንቲ ተወካይ ድርጅቶች፣ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የበጎአድራጎት ቡድኖች እና ሌሎች ጋር ሽርክናዎች አዳብሯል። ይሁንና ተማሪዎቻችን በወደፊታቸው ለመበልፀግ ዝግጁ መሆናቸውን እንድናረጋግጥ ከሆነ ማህበረሰቡን ማሳተፍና አቅምም እንዲኖረው ማድረግ ይበልጥ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## ፕላኑ

ልጆቻችንን ለስኬት ከማዘጋጀት ጋር በተያያዘ፣ ተማሪዎችን በማገልገል ላይ የሚገኙትን ሽርክናዎች ለማስፋፋት እና ቤተሰቦችን፣ የማህበረሰብ አባላትን፣ የንግድ ድርጅት መሪዎችን የሚያሳትፉ ሙያተኞች ለመቅጠር፣ የቦርዱ በጀት $800,000 ያካትታል። እነዚህ ገንዘቦች የሚያስችሉት—

- የKennedy Cluster ፕሮጀክትን ወደ Watkins Mill Cluster መስፋፋት መደገፍ። ፕሮጀክቱ ተማሪዎችንና ቤተሰቦቻቸውን በትምህርት፣ የጤና እንክብካቤ፣ መኖርያ ቤት፣ የፋይናንሳዊ ድጋፍ፣ የህግ እርዳታ፣ እና በሌላም ድጋፍ የማግኘት እድል ያቀርብላቸዋል። ተጨማሪ ገንዘብ በካውንቲው በኩል ይቀርባል።

- በስድስት የMCPS የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከትምህርት ሰአታት በኋላ ከፍተኛ ጥራት ያለው ፕሮግራም አቅራቢ በሆነው በExcel Beyond the Bell (ከደወል በኋላ ልቀህ ተገኝ) እንዲሳተፉ ለተማሪዎች ተጨማሪ መኳኋሻ ማቅረብ። ፕሮግራሙ የMCPS፣ የMontgomery County Collaboration Council (የትብብር ምክር ቤት)፣ እና የMontgomery County Department of Recreation (የመዝናኛ መምርያ)፣ እንዲሁም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የንግድ ተቋሞች የትብብር ጥረት ነው።

- ለወላጆች አገልግሎት እና ከማህበረሰብ ጋር ተሳትፎ ለሚያስፋፋው ለOffice of Community Engagement and Partnerships (የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ሽርክና ፅ/ቤት) የወላጅ ማህበረሰብ አስተባባሪዎችና ሌሎች ሰራተኞች መጨመር።

## እወቁ/ተማሩ፣ ተገናኙን

በቦርዱ ስለቀረበ በጀት በMCPS ድርጣብያ www.montgomeryschoolsmd.org "Operating Budget" በመፈለግ ይበልጥ መማር ይችላሉ። በጀቱ አሁን በMontgomery County ስራ አስፈፃሚ እና በMontgomery County ምክር ቤት እጅ ይገኛል። ሀሳብዎን ከነሱ ጋር ይጋሩ፡

- Montgomery County ስራ አስፈፃሚ Isiah Leggett (አዛያህ ሌጌት): ocemail@montgomerycountymd.gov፣ 240-777-2500

- Montgomery County ምክር ቤት፡ county.council@montgomerycountymd.gov፣ 240-777-7900



MCPS